# የውሸት ዘመን - ክፍል ሁለት

(ማወቅ ይበጃል 16-07-2010)

<u>**ማስታወሻ :-**</u> ከ1-4 ያሉት ርዕሶች ክፍል አንድ ላይ ይመልከቱ።

## 5. የኢህአዴግ የመተካካት ውጤት

በመርህ ደረጃ ኢህአዴግ ከአንጋፋው ትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ በታቀደ መልኩ የሃላፊነትና የስልጣን ሽግግር እንዲኖር ማድረጉ የሚደገፍ ተግባር ነው። በተጨማርም የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ እንድቻል በቀጥይነት ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው። አሁን ካለው አንጋፋ የኢህአዴግ አመራር ወደ አዲሱ ትውልድ የፖለቲካ አስተሳሰቡ ማስተላለፍና ከወዲሁ ቀጣይነቱ ማረጋገጥ ለአፍታም ችላ መባል የሌለበት ጉዳይ ይመስለኛል። የፖለትካ ትግል እንደ የዱላ ቅብብሎሽ ሩጫ መሆኑ የሚታወቅ ነገር ነው። ስለዚህ የኢህአዴግ አንጋፋ ከፍተኛ አመራሮች ከነሱ ሥር የአመራር ክህሎት እያዳበሩ የመጡ ሰዎች ይሁኑ ሌሎች ምሁራን የፖለቲካ ሃላፊነታቸው ማሸጋገራቸው ሁላችንም የሚያግባባ መልካም አስተሳሰብ ነው።

ነገር ግን የመተካካት ስትራተጂና ሂደቱ ጥንቃቄ የሚሻ ጉዳይ መስሎ ታይቶኛል። ተኪ ተብለው የሚመለመሉና የሚታጩ የድርጅቱ የአመራር አባላት የአቅምና የአስተሳሰብ ደረጃቸው በውል ሊጠና ይገበዋል። ተኪ የአመራር አባላት በሚመዘኑበት ጊዜ የትምህርት ዝግጅትና የፖለቲካ አቅማቸው፤ የመወሰን፣ የመፃፍ፣ የመተንተንና የመግለፅ አቅማቸው፤ የአመራር ችሎታና ህዝብን የማስተዳደርና የማገልገል ዝግጁነታቸው፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአቋማቸው የማይዋዥቁ ስለመሆናቸው ወዘተ በከፍተኛ ጥንቃቄ መታየት አለበት። ምናልባት ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ተኪዎች የማፍራት አሠራርና ስትራተጂ ይኖሮዋል ብየ አምናለሁኝ። ነገር ግን አሠራሩና ስትራተጂው የሚፈተነው እነዚህ ተኪዎች ስልጣን ላይ ተቆናጥጠው ህዝብን ማስተዳደር ሲጀምሩ በሚኖረው ለውጥ ነው። ለውጡ ገምቢ ነው ወይስ አፍራሽ አንድ ጉዳይ ሁኖ ችግሮች በሚፈጠሩበት ጊዜ አፈታታቸው ስንመረምረው አቅማቸውና የፖለቲካ ውግንናቸው ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ተኪዎች የሚያመጡዋቸው የመፍትሄ ሃሳቦች እዚህ ግባ የማይባሉ፣ በህዝቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው ከሆኑና ነገሮች በፍጥነት በወጉ ውሳኔ ሳያርፍባቸው ቀርተው በይደር እየተንከባለሉ ህዝቡ ለእንግልትና ለተቃውሞ የሚያጋልጡ ከሆኑ መተካካቱ መሠረታዊ ችግር አለበት። በዚህ መነፅር አሁን ያለው የሀገሪቱ የፖለቲካ አለመረጋጋት ከምክንያቶቹ አንዱ የኢህአዴግ የመተካካት ችግር ነው ብዬ አምናለሁኝ።

ይህን የህዝብ ትግልና ሥርዓት መርተው እዚህ ያደረሱ አንጋፋ የኢህዴግ አመራሮች የትግል ስልት የቀየሱት ፤ የሀገር ግንባታ (nation building) ስትራተጂ የዘየዱትና የነጠረ የፖለቲካ ሥርዓትና ዓላማ ያረቀቁት ከኢትዮጵያ ህዝብ ነባራዊ ሁኔታ ባሻገር ምናልባትም በጣም ጥቅት መፃህፍትና ሰነዶች ታግዘው እንደሚሆኑ ግልፅ ነው። እነዚህ አንጋፋ አመራሮች ትግል የጀመሩት እንደ አሁን ዓለም በመረጃ ጎርፍ በተጥለቀለቀችበት ጊዜ ሆነው ሳይሆን መረጃ በመፃህፍትና ጋዜጦች ተጠናቅሮ እየተቆነጠረ በሚለቀቅበት ጊዜ ነበር። ዛሬ መረጃ በመዳፋችን ላይ በተለያየ መንገድ በቀላሉ መግባት በምችልበት ጊዜና

ሁኔታ ሆነው አንጋፋዎችን በመተካት ሃላፊነት የተሰጣቸው ልፍስፍስ አመራሮች የአቅም ውሱንነትና ሃሳብ የማፍለቅ ድህነታቸው ለኔ ጎልቶ እየታየኝ ነው።

ባለፉት ዓስርት ዓመታት ኢህአዴግ በመተካካት ስም ወደ አመራርነት ያመጣቸው ግለሰቦች የተወሰኑትን ትቶ በአብዝሃኛዎቹ ብትጨምቃቸው፣ ብትጨምቃቸው የአንዲት ጠብታ ዕውቀት እንኳ የሚወጣቸው አይመስሉም። አንዳንዶቹማ በዘፈቀደ የሚነጉዱ፣ እንደ መሰላቸው የሚነፍሱ የዘቀጠ የትምክህትና የቀለም አብዮተኞ አስተሳሰብ ማከማቻ ናቸው። የተወሰኑት ደግሞ ስትመለከታቸው በአቅም ደረጃ አስተሳሰባቸው ደህና ሆነው በኢህአዴግ መርህና የፖለቲካ እምነት በደምብ ያልተገሩ መሆናቸው ትገነዘባለህ። አለፍ ብለህ ደግሞ መሠረታዊ በሚንለውም መሪህ የማይገዙና የአመራር ዲሲፕሊን የሌላቸው ህዝበኞች (populist) ሆነው ታገኛቸዋለህ። የሚገርመው ነገር አንድ ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ሁላችንም የመፍትሄ ሃሳብ ከአንጋፋዎቹ የኢህአዴግ አመራሮች እንጠብቃለን። ኢህአዴግ በማዳን ጉዳይም ተኪና ተተኪ የተፋጠጡበት ጊዜ ይመስላል።

በትክክል እንመልከተው ከተባለ አሁንም የህዝቡ እምነት ያረፈው በአንጋፋዎቹ ላይ ነው። በነ አቶ ካሳ ተክለብርሃን (ለምን እንኳ ወደ አሜሪካ እንደላኳቸው?)፣ በነ አቶ አዲሱ ለገሰ፣ እነ አቶ አባይ ፀሃየ፣ በነ አቦይ ስብሓት፣ በነ አቶ ኩማ ደመቅሳ ወዘተ (ሁሉም ከሚዘረዝር) ላይ የህዝቡ እምነት የተሻለ ሁኖ ታገኘዋለህ። ተኪዎቹማ ጎራ ለይተው የሚጠፉፉ ነው የሚመስሉት። የሻዕብያ፣ የትምክህትና የጠባብ ኃይሎች ምድያዎች የሚያጠቁት አንጋፋዎቹ የኢህአዴግ አመራርን ነው። አንጋፋዎቹ የኢህአዴግ አመራር ተዳክመው ከወደቁ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ተከዎቹ ከቁጥር አያስገቧቸውም። በአንድ አስተሳሰብ ራሳቸውን አኑሮው መራመድ የማይችሉና በስሜት የሚነዱ ልፍስፍሶች መሆናቸው ነቅተውባቸዋል። ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን በማፈራረስ አጀንዳቸው ላይ በቀላሉ ሊያሰልፏቸው እንደሚችሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ተወደደም ተጠላም ኢህአዴግ መቀበል ያለበት ባለፉት ዓመታት የታየው የአመራር ክፍተትና ድክመት የመተካት ስትራተጅው ግድፈት ውጤት መሆኑ ነው።

እኔ የኢህአዴግ ጠንካራ ደጋፊ ነኝ - ከኢህአዴግ የተሻለ የፖለቲካ ድርጅት እስካልተፈጠረ ድረስ። በክፍል አንድም ይሁን በዚህ ክፍል ኢህአዴግ ላይ የታዩኝ ጉድለቶች አንስቻለሁኝ። ደጋፊ ከሆንክ ለምን ትሉኝ ይሆናል። መደገፍ ማለት እንደ አዝማሪ መልካም፣ መልካሙን መዘመር ማለት አደለም። በርግጥ ኢህአዴግ ለዚህ ችግር የዳረገው መልካም፣ መልካሙን መስማት መፈለጉን ይሆናል። መልካም፣ መልካሙን የሚዘሙሩለት ሰዎች አቀረበ። ለማንኛውም በኔ እምነትና ግንዛቤ ለመተካካቱ ችግር መንስኤ ናቸው ያልኳቸውን ነጥቦች እንደሚከተለው ተቀምጠዋል።

1. መጀመርያ የችግሩ መንስኤ ራሳቸው የኢህአዴግ አንጋፋዎቹ አመራሮች ናቸው። ትክክለኛ ተኪ የማፍራት ሃላፊነት በዋናነት የነሱ ስለሆነ። በኢህአዴግ መርህና የፖለቲካ እምነት (አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ) ተኪዎች የመግራትና የማነፅ ሃላፊነት የወሰዱና መውሰድም ያለባቸው እነሱ ስለሆኑ። ታድያ በነሱ ሥር ያሳደግዋቸው ሰዎች አንድም ወሬ አቀባይ በራስ መተማመን የሌላቸው “አብየት ጌታዬ” ዓይነት ሰዎች ናቸው። አልያም የኢህአዴግን ዓላማ የሚንዱ ኃይሎች የኢህአዴግ ጃኬት (ኮት) ለብሰው ከአንጋፋዎቹ የኢህአዴግ አመራሮች ሥር በሚገባ ተደግፈው አድጓል ።
2. ሌላው ነጥብ በኢህአዴግ ውስጥ የተለመደ አፍራሽ መዋቅር ስውር የአመራሮችና የአባላት ኔትወርክ ነው። በመሠረቱ ይህ ስውር የኔትወርክ መዋቅር ሁነኛ የስልጥናቸው መከላከያ መሳርያ ነው። ይህ ስውር የኔትወርክ አወቃቀር እርስ በርሱ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይ እየተመጓገሰ በህዝቡ አስተሳሰብም ፍፁም የተሳሰተ ገፅታ

እየፈጠረ ጥቅሙና ስልጣኑ የሚያረጋግጥ፣ የህዝብ ጉዳይ ወደ ጎን የተወ ነው። ይህን ኔትወርክ የሚመሠረተውና የሚያድገው በዋናነት የትውልድ መንደርን መሠረት በማድረግ ነው። ከዛም አልፎ በሙስና የህዝብን ገንዘብ በማግበስበስ ላይ የሚገናኙ ሃላፊዎችም ይመሠሩትታል። የኔትወርኩ ዋና ዓላማ ጥቅምንና ስልጣንን የመከላከል አጀዳ የያዘ ነው። የመተካካት አጀንዳም ሲነሳ ሁሉም ከራሱ ኔትወርክ ይተካል። በነገራችን ላይ በኔ እምነት በአሁኑ የኢህአዴግ የጥልቅ ተሃድሶ እንቅስቃሴ ኔትወርክ በማፈራረስና ራሱን በትክክል በመገምገም ጥሩ ርቀት የሄደው ህወሓት ነው። አሁን ወደ ሥራ አስፈፃሚነት የመጣው የህወሓት አመራርም በጥንቅሩ ደህና ይመስላል።

3. በሶስተኛ ሊነሳ የሚችለው ነጥብ በቅርብህ ያለው በተወሰነ የሥራ ሃላፊነት ረዘም ላሉ ዓመታት ከአንተ ጋር የሠራ ግለ ሰብ ከፍ ያለ የሃላፊነት ቦታ እየሰጠህ መሄድ ደግሞ የተለመደ ነገር ነው። የግለሰቡ ብቃት መሰረት ያደረገ ሳይሆን አመራሮች ከግለሰቡ ጋር በጊዜ ሂደት አብሮ በመስራቱ ምክንያት በሚያዳብሩት እምነትና ሰብአዊ ትስስር መሠረት በከፍተኛ የሃላፊነት እርከን እንዲቆናጠጥ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ጉዳይ በሰፊው ይታያል።
4. ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ጥሩ ሰዎች የማደን ዝንባሌ አልተገነዘብኩለትም። ጥሩ ጭንቅላት ያላቸው (best minds) በማደን በአስተሳሰብና በፖለቲካዊ የአመራር ዲሲፐሊን አንፆ በሀገሪቱ ጉዳይ ላይ ማሳተፍ አስፈላጊ ነው ብየ አምናለሁኝ። እንድያውም በኢህአዴግ አባልነት የሚመዘገቡ ሰዎች በሥራ ዓለም ሰነፍ የሆኑና በዩኒቨርስቲ በትምህርት አቅማቸው ዝቅተኛ የሆኑ ናቸው ይባላል።

## 6. የውሸት ዘመንና የኢትዮጵያ ጠላቶች

የማህረዊ ሚድያ ተጠቃሚ በጣም እየጨመረ በመጣበት ጊዜና የግንኙነት ቴክኖሎጂ እያደገ በመጣበት ጊዜ በተንኮል የተተበተበ የሃሰት መረጃ በወጣቶች መዳፍ ላይ ማድረስ በጣም ቀላል ሁኑዋል። ሻዕብያና ግበረአበሮቹ እንዲሁም ፅንፈኛ ዲያስፖራ ፖለቲከኞች ይህን አፍራሽ መንገድ በመከተል በኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ላይ አስቸጋሪ ፈተናዎች ለመደቀን ወጥረው እየሰሩ ይገኛሉ። ህዝቦች ስሜታቸውን ሊቆረቁር የሚችል ታስቦበት ዲዛይን የተደረገ የጥላቻ ይዘት በተደራጀ መልክ ይረጫሉ፣ ያሰራጫሉ። በደምባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ እንደሚባለው መንግስት በራሱ በፈጠረው የውስጥ ችግር ላይ እንደ ሻዕብያና ማስተሮቹ የሚያሰራጩት የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ተጨምሮ አገራችን የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ እየከተታት ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ተጋላጭ የሆነችበት ጉዳይ የቀለም አብዮተኞች ጥቃት ነው። በተለያዩ ፅሁፎች እንደተገለፀው የቀለም አብዮት ምዕራባዊያን ወይም ደግሞ የኒኦ ሊበራል ኃይሎች በጎዳና ላይ ነውጥና አመፅ በማቀጣጣጠል መንግስትን ለማፈራረስ የሚጠቀሙበትና የዓለም ሉዓላዊ ህዝቦችን የሚያጠቁበት፣ የሚቆጣጠሩበትና አንጡራ ሀብታቸውን የሚበዘብዙበት ስልት ነው። የቀለም አብዮት ከቀድመዋ ሶቭየት ኅብረት ጀምሮ በብዙ አገራት በተከታታይነት የተሞከረ በአንዳንዶቹ የመከነ በአንዳንዶቹ ደግሞ መንግስት አልባ አገሮች የፈጠረ አደገኛና አፍራሽ ተግባር ነው። በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው የቀለም አብዮት ነው ወይ ሌላ ጉዳይ ሆኖ ኢትዮጵያ ለቀለም አብዮት ተጋላጭ መሆንዋ ግን በግልፅ ማየት እንችላለን።

ኢትዮጵያ ለዘመናት ለነጮች (ምዕራባዊያን) ለአፍታ እንኳ ሳትንበረከክ ለአፍሪካዊያን ነፃነት ተምሳሌት መሆንዋ፣ ዛሬ ደግሞ የራሱ የሆነ ለየት ያሉ ባህርያት ያሉት ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት መገንባት መቻልዋና በራሱ የሚቆም የኢኮኖሚ (self-resilience economy) ግንባታ ለማካሄድ ቁርጥኛ መንገድ መያዝዋ ለምዕራባዊያን ኒኦ ሊበራል ኃይሎች እረፍት የሚሰጥ

አይመስለኝም። ኢትዮጵያ አሁን በያዘችው መንገድ ተግዳሮቶችን አልፋ ውጤት ማስመዝገብ ከቻለች ሌሎች አፍሪካዊያን ሀገሮች ተመሳሳይ መንገድ የማይከተሉበት ምክንያት የለም። አፍሪካዊያን አንጡራ ሃብታቸውና የመዋዕለ ንዋያቸው ፍሰት መቆጣጥር ቻሉ ማለት ለኒኦ ሊበራላዊያን ራስ ምታት ከመሆን አልፎ ጥቅማቸው በእጅጉ የሚጎዳ ነው። በዚሁ ምክንያት የኒኦ ሊበራል ኃይሎች ኢትዮጵያን በቀለም አብዮት ጦራቸው ለመውጋት ዘወትር ዝግጁ መሆናቸውን እኛ ኢትዮጵያዊያን በተለይ ወጣቶች በደምብ መገንዘብ አለብን። የቀለም አብዮት አራማጅ ኃይሎች እንደ መሳርያ የሚጠቀሙበት ኃይል በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና የዓለም ሁኔታ ግንዛቤው ያልዳበረ አፍላ ወጣት ነው። በስመ ዲሞክራሲ፣ ሰብአዊ ሙብትና ኢፍትሃዊ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ያነሳሱታል።

የኒኦ ሊበራሊዝም ኃይሎች የቀለም አብዮትን ለማነሳሳት የሰብአዊ ሙብት ተሟጓች ድርጅቶች፣ የርዳታ ድርጅቶችና እንደነ አልበርት አንስታይን ተቋም የመሳሰሉት የምዕራባዊያን አደገኛ ያልታጠቁ ኃይሎች ይጠቀማሉ። እናስተውል! ኢትዮጵያ በሰብአዊ ሙብት ረገጣ በሁማን ራይትስ ዎች (Human rights watch) በተደጋጋሚ ይከሷታል። ነገር ግን በራሳቸው መንግስት ከፍተኛ የሰብአዊ ሙብት ረገጣ ይካሄዳል። ሰዎች በቀለማቸውና በዘራቸው ከፍተኛ ተፅኖ ይደርስባቸዋል። ሰላማዊ ሰዎችና ህፃናት ሳይቀሩ በአደባባይ በጅምላ ይገደላሉ። ያገራቸው ሰላም ሳያረጋግጡ ስለኛ ሰላም የተጨነቁ ይመስላሉ። በታላላቅ ምድያቸው በኢትዮጵያ 6% የሚሆነው የትግራይ ህዝብ የፖለቲካ ስልጣኑና ኢኮኖሚው እንደተቆጣጠረው በማስመሰል በውሸት ያወራሉ። በራሳቸው ሀገር ግን የህዝባቸው 1% የሚሆነው የሀገሪቱ ሀብት ተቆጣጥሮታል። በነሱ ሀገር ጥቁሮች በፖለቲካ ስልጣን ያላቸው አስተዋፅኦ በጣም ዝቅተኛ ነው። በሙቶ ዓመታት ውስጥ አንድ የጥቁር ዘር (ፕረዚደንት ኦባማ) ፕረዚደንታዊ ስልጥና በመያዙ ተአምር ተብለዋል። ስለዚህ አጀንዳቸው የሰብአዊ ሙብት ጉዳይ አይደለም። ለያንዳንዳችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታችን ጉዳይ አሳስቦቸውም አይደለም። ዓላማቸው አንድና አንድ ነው። እንደፈለጉት የሚጠመዘዙት መንግስት ስልጣን ላይ አስቀምጠው ኢትዮጵያ ብሎም አፍሪካ በነርሱ ርዮተ ዓለም ሳጥን ውስጥ ከተው የአፍሪካን ሀብት በማያቋርጥ መንገድ መዛቅ ነው።

የሻዕብያና የስፖንሰሮቹ ዓላማም እንመልከት። ሻዕብያ ኢትዮጵያን በኢትዮጵያዊያን ለማጥፋት ስልት መቀየስ ከጀመረ ዓስርት ዓመታት አስቆጥሮዋል። ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ የቀየሰው ስልት ግን በጣም አደገኛ ነው። በራሱ በኢሳያስ አፈዎርቅ የሚመራ ኢትዮጵያን የማተራመስ ተልኮ ያነገበ አንድ የተደራጀ የጥፋት ኃይል ፈጥረዋል። የዚህ የተደራጀ ኃይል ዋነኛ ተባባሪዎች ግንቦት 7 እና ኦነግ የመሳሰሉ የጥፋት ኃይሎች ናቸው። የነዚህ ኃይሎች ማለትም ሻዕብያ ያደራጀው የውስጥ ኃይል፣ ኦነግና ግንቦት 7 ተልዕኮቸው ለማስፈፀም የሚያስችላቸው ገንዘብ የሚፈሰው በዋናነት ከግብፅ ቢሆንም ሌሎችም እንደሚኖርበት ይገመታል። የተልኮቸው ዋነኛ ማጠንጠኛ የትግራይ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ማጣላትና ማግለል የሚቻልበት መንገድ መፍጠር ነው። ከዛም አልፎ የኢትዮጵያ ህዝቦች እርስ በራሳቸው በማናቆር የተተራመሱችና በእርስ በርስ ጦርነት የተዳከሙች ሥርዓትና መንግስት አልባ ኢትዮጵያ መፍጠር ነው።

ሻዕብያ እንደ የመጨረሻ ዕላማ ያደረገው አያሳልፈኝም ብሎ ያሰበውን የትግራይ ህዝብ በማዳከምና በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ እንዲገለል በማድረግ አፈንግጦ በራሱ ተፅኖ ሥር እንዲወድቅ ማድረግ ነው። ከዛም አልፎ በሻዕብያ መንግስት ተፅኖ ሥር የወደቀ መንግስት በኢትዮጵያ በመፍጠር ወይም ይህ ካልሆነ የተበታተነች ኢትዮጵያ በመፍጠር የኢትዮጵያን ሀብት እንደፈለገ ለመመዝበር ነው። ለዚህ ዓላማ ለማሳካት ፍላጎት ያላቸውን ኃይሎች በየፊናቸው አሰባስበዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በራሱ ለማቃቃር የሚያስችላቸው ዘዴም ዘይደዋል። ኦሮምያ ውስጥ ወጣቱ ምን ብለው ኮርኩረው ስሜቱ

እንደሚያነሳሱት፣ የአማራ ወጣትም በምን መንገድ በስሜት እንደሚያነሳሱት እንዴት በትግራይ ተወላጅ ላይ እንደሚያነሳሱት በደምብ አጥንተው ገብተውበታል።

በዚህ የውሸት ዘመን ይህ መሰሪ የሻዕብያ ጥንስስ ተንኮል ለማሳካት ስታሰብ ምን እንደተፈፀመ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። አነግ ውስጥ ውስጡን የኦሮምያ ወጣቶች የሚያነሳሱለት ሰዎች አደራጀ (በወር ብር 4500 እንደሚከፈላቸው ይነገራል)። ግንቦት 7 እሳት በተባለ የተለቨቨን ሚድያ በትግራይ ህዝብ ላይ የተለመደው የጥላቻ ዘመቻ በበለጠ በማጣጧፍ እስከ የዘር ማጥፋት እወጃ አወጀ። ሻዕብያም እነ ጀዋር መሃመድን የመሳሰሉ የኢንተርኔት activist ቡድን ጋር በመቀናጀት የራሱን የማህበራዊ ሚድያ ሰራዊት አዋቀረ። እነዚህ የሻዕብያ የማህበራዊ ሚድያ ሰራዊት አንዴ ኦሮሞ፣ ቆይተው ደግሞ አማራ፣ ቀጥለው ተጋሩ እየሆኑ በተለይ ሶስቱ ህዝቦች የሚያናቁሩ የጥላቻ ንግግሮች እየፈበረኩ ጦርነታቸው ቀጥለዋል። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት የፖለቲካ ቀውስ ደረሰች።

በኔ እምነት የኢትዮጵያ ጠላቶች በዚህ መልክ መለየት ይቻላል። የኢትዮጵያ ጠላቶች በቀለም አብዮት ማራመድ የሚታወቁት የኒኦ ሊበራል ኃይሎች፣ ኢትዮጵያዊያን የትምክህትና የጠባብ ኃይሎች፣ የሻዕብያና የግብፅ ጥምር ኃይሎች ናቸው። እንዚህ ኃይሎች በማያዳግም መመከትና ሀገራችንን ማዳን የእያንዳንዳችን ኢትዮጵያዊያን ሃላፊነት ቢሆንም አንድ ማሳሰብ ያለብኝ ጉዳይ አለ። የቀለም አብየተኞችና ሌሎች የውጭ ኃይሎች የማተራመስ ውጥናቸው የሚሰምረው በሀገራችን ውስጥ ልፍስፍስ አመራርና ሊፍስፍስ መንግስት ሲኖርና የህዝብ አስተዳደር ስበላሽ ነው። በኔ ግምገማ የሀገራችን ተቋማት ጠንክረው እየወጡ ነው። በተለይ ደግሞ የመከላከያ፣ የደህንንነትና የፌደራል ፖሊስ ተቋሞች አድናቆት ሊንችራቸው ይገባል። እነዚ ተቋማት ህገ መንግስታዊ ተልኮቸው ሳይሸራርፉ መሬት ላይ ካዋሉት የቀለም አብዮተኞች መፈናፈኛ ቦታ የላቸውም። በጣም ያዛዘነኝ ግን የፖለቲካ አመራር ኃይሉ መልፈስፈሱ ነው። ያዛዘነኝ ነገር የሻዕብያ መሰሪ ተንኮል በተወሰኑ የኢህአዴግ አመራር አባላት መስረፅ መቻሉ ነው።

ራሽያ፣ ቻይና፣ ኢራን ወዘተ በቀለም አብዮት ሊሙቱ ይፈለጋሉ። ነገር ግን በየሃገራቱ ባለው የመንግስት ጥንካሬና የመከላከል ስትራተጂ ምክንያት የቀለም አብየተኞች በራቸውም ድርሽ አይሉም። ስለዚህ በኛም ሀገር የቀለም አብዮተኞች ጥቃት ከሩቁ መግታት አለብን። የቀለም አብዮተኞች ጥቃት ከሩቁ ለማስቀረትና የሻዕብያና ግብረ አበሮቹ ሴራ ለማክሸፍ ኢህአዴግ በአሁኑ መድረክ ከሚንጠብቅበት በላይ ጠንክሮ መውጣት አለበት። ለውጭ ኃይሎች በቀላሉ የሚያጎበድዱ እንክርዳድ አመራሮቹ ለይቶ ማስወገድ አለበት።

ይህ ካልኩ ዘንዳ ለኢትዮጵያውዊያን ወጣቶች በተልይ ደግሞ ለቄሮዎች የማስተላልፈው መልክት አለኝ። እኛ ሀገራችን ኢትዮጵያ ናት። ኤርትራም የኤርትራዊያን ወድሞቻችን ናት። ግብፅም የግብፆች ናት። ምዕራባዊያንም ቆርሰው የሚሰጡን መሬት የለም። የኛ የሆነውን አፍርሰን፣ ኢቃጥለን ፤ የኛ ባልሆነው ተሰደን ለመኖር ብንመኩር ከፍተኛ ውርደት ይገጥመናል። የሶርያዊያን ዕጣ ፈንታ ማየቱ ይበጃል - የሶርያዊያን እናቶችና የሶርያዊያን ህፃናት ዕጣ ፈንታ። ቤቱ የሚያቃጥልና የሚያፈርስ ማደርያ የለውም። ከላይ የዘረዘርኳቸው የኢትዮጵያ ጠላቶች ለማስደሰት ማደርያችን የሆነችው ኢትዮጵያ አናቃጥል። ተቋሞችዋ አናቃጥል፣ መንገዶችዋ አንዝጋ አናፍርስ፣ የኢኮኖሚ አውታሮችዋ አናዳክም፣ ከሁሉም በላይ ህዝቦችዋ አንጉዳ። ብታምኑም ባታምኑም በያንዳንዱ በጎ ድርግት አርቆ አሳቢነትና ዕውቀት አለ። በያንዳንዱ መጥፎ ድርግት ወይ የተመረዘ ዕውቀት አልያም ሰፊ የመረጃ ግድፈት አለ። በማወቅ ላይ ትዕግስት አለ፤ በትዕግስት ላይ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የማሸነፍ ኃይል አለ። ለዚህ ነው ማወቅ ይበጃል ያልኳችሁ። ስለዚህ ለምንወስደው ሃላፊነት ሁሉ ጠንቅቀን በማወቅ ይሁን።

ከላይ አጠር ባለ መልኩ የኢትዮጵያ ጠላቶችና ዓላማቸው የዘረዘርኩበት ምክንያት በአመፅና ነውጥ እየተሳተፈ ያለ ወጣት የነሱን አጀዳ እያስፈፀመ መሆኑ ለማስታወስ ፈሊጌ ነው። በተለይ ቄሮዎችና የአማራ ወጣቶች ዋናው ወገናችሁ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነው ህዝባችሁ ነው። በትዊተር (twitter) ገፅ እየፃፉ አጥፊ መመርያ (command) የሚለቁልላችሁ ግለሰዎች የናንተ አጀንዳ ሳይሆን የጠላቶቻችን አጀንዳ ነው ያነገቡት። ከነጀዋር መሃመድ ጀርባ ያሉ አጥፊ ኃይሎች ለማወቅ ሞክሩ። ቢታምኑም ባታምኑም ጀዋር መሃመድ ኢትዮጵያን በማተራመሱ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ ዶላር ይከፈለዋል። ከሱም አልፎ አገር ውስጥ ያሉ የሚያነሳስዋችሁ ኃይሎች ከፍተኛ ብር ይከፈላቸዋል። ኢትዮጵያ ሜጋ ፕሮጀክቶችዋን እንዳታከናውንና በዲሞክራሲና በኢኮኖሚ እናዳትበለፅግ የሚፈልጉ ኃይሎች የጀዋር ስፖንሰሮች ናቸው። እናንተም የነሱ ተባባሪ ሁናችሁ ሀገራችሁን ማፍረስ ፈለጋችሁ? ራሳችሁን ጠይቁ።

ዕውቀት በማዳበርህ ትዕግስት እንደሚታዳብረው ሁሉ ቄሮዎች ማስታወስ ያለባችሁ ነገር ቢኖር በትዕግስት ውስጥ ታላቅነት እንዳለ ነው። በትዕግስት ውስጥ ነገሮችን በትክክል የማወቅ፣ የመመርመርና፣ የመረዳት ሰፊ ዕድል አለ። ማወቅ ማለት ያልለፋህበት የሃሰት ዶክትሬትና ዲግሪ መሰብሰብ ማለት አደለም። ማወቅ ማለት በትክክል መማር፣ ማንበብና መመራመር፣ እንዲሁም እውነትን ከተቆለፈት ፈልቅቆ ማውጣት ማለት ነው። ስም እያመሳሰሉ "ፀሓይ ሪል ስቴት የአባይ ፀሃየ ነው ስሏችሁ" እውነታ እንዳለው ጉዳይ ከመቀበላችሁ በፊት በየትኛው ማስረጃ አረጋገጣችሁት? ለማንኛውም የነጃዋር ፀሃይ የመታው ውሸትና ከጀርባው ያሉ አጥፊ ኃይሎች ላም ነጂዋን እንጂ ባለቤታዋ አታቅም ዓይነት እንዳይመስል ማወቅ ይበጃል!

## 7. "ማን ሠራው ቢባል ማን ሠራው ሊባል ነው?"

በዚህ የውሸት ዘመን ኢትዮጵያ የሚገርም ዓይነት ፅንፈኝነትም እያስተናገደች ትገኛለች። በቅርቡ አንድ በፅንፈኞች የተፃፈ የነውጥ ማፅበል ምንትሴ የሚል መፅሃፍ ካስነበበን አንዱ ዐረፍተ ነገር "በደማቸውም ግድብ ብገነቡልን እንኳ አንቀበልም" ይላል። ነገርየው ለተጋሩ መሆኑ ነው። ታላቁ የህዳሴ ግድብ ከሆነ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰዎችና ህዝቦች በመላ በአንድ ቃል ተስማምተው በራሳቸው የገንዘብ አቅም አቫራቸው እያኖሩ እየገነቡ ያለ ግድብ ነው። ፀሃፊው ኢትዮጵያዊያን ህዝቦች የገነቡት ግድብ አልቀበልም ካለ ታድያ ማን ይገንባልህ የሚለው ጥያቄ መቅረቡ አይቀርም። ግብፅ ወይም ሻዕብያ ይሉን ይሆን። ነገሩ ፀሃፊው በሸዋ ገዢ መደቦች ተገነባ ተብሎ ካልተነገረለትና ካልተፃፈለት አልቀበልም ማለቱ ነው።

የግዛት አንድነት አራማጆች በዚህ ዘመን ፈፅሞ ይታሰባል ብለህ የማትገምተው ያረጀ የፈጀ አስተሳሰብ ይዘው ሲማጉቱ ብዙ ጊዜ ያስገርመኛል። በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ተቀባይነት ያገኘውና ዕውቅና የተቸረው የሀገራችን ኢኮኖሚያዊ ለውጥ በጭፍን ምንም ለውጥ የለም ይላሉ። የተሰራውም በዲዛይን፣ በጥራትና በመሳሰሉት ነገሮች ለማንቋሸሽ ይሞክራሉ። የህዳሴ ግድም ጉዳይም ሲነሳ አንዴ በአፄ ሃይለሲላሴ ዲዛይን የተደረገ ነው ይላሉ፤ አንዴ ደግሞ መንግስቱ የጀመረው ነው ይላሉ። ይዘባርቃሉ፣ ይዘባርቃሉ . . . አሁንም ይዘባርቃሉ ይቀጥላሉ። ለዚህ ሁሉ ጭንቀታቸው የኢትዮጵያ ህዝቦች ተባብረው የመሰረቱት የኛ የሚሉት ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት ዕውቅና ላለመስጠትና የፌደራሊዝሙ ትሩፋቶችና መልካም እሴቶች ለማንቋሸሽ ነው። የፌደራል ሥርዓቱም አልሰራም እንዲባል ዘንድ ያለው እውነታ መካድና የፌደራል ሥርዓቱ የልማት ውጤት የሆኑ ነገሮ ች ሁሉ ማንቋሸሽ ይቀናቸዋል። ይባስ ብለውም ከሻዕብያና ግብፅ ተባብረው የልማት ሂደቱ ለማደናቀፍ ያለእረፍት እየሠሩ ይገኛሉ።

በአንድ ወቅት 1997 ዓ/ም አንድ ወገኔ ሚኒ ባስ ታክሲ ላይ ተሳፍሮ በቀለበት መንገድ ላይ ጉዞ ይጀምራል። ሰዓቱም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አከባቢ ነበር። ከተቀመጠበት ወንበር ፊት ሁለት ትላልቅ ሰዎች ተቀምጧል። በተለይ በዚያን ጊዜ መንገዱ አንዳንድ ብልሽት ሳይደርስበት ስለነበረ፤ በምሽት ስትጓዝበት ከመብራቱ ጋር ተቀናጅቶ በጣም ያምር ነበር። ከትላልቅ ሰዎቹ አንዱ "መንገዱ እንዴት ያምራል ባክህ! አውሮፓ እኮ ነው ያስመሰሏት።" አሉ። ከጎናቸው የተቀመጡት ጓደኛቸው "ታድያ ምን ዋጋ አለው?" ብለው ጥያቄቸው ሰነዘሩ። ጓደኛቸውም አከታትለው "ምነው?" ብለው ጠየቁ። ጥያቄውን በጥያቄ ሲመልሱ "ማን ሠራው ቢባል ማን ሠራው ሊባል ነው ?" አሉ። መቸም ሰውየው ምን ማለት እንደፈለጉ ለሁላችንም ግልፅ ነው። ከኃላቸው የተቀመጠውና በንግግራቸው ያዘነው "ጌታዬ ማን ሠራው እንዲባል ይፈልጋሉ ?" አላቸው። መልስ አላገኘም። "ማን ሠራው ቢባል ማን ሠራው ሊባል ነው ?" ለሚለው የሰውየው ጥያቄ መልሱ ግልፅ ነው። የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰዎችና ህዝቦች ሠሩት። መንገዱም፣ ግድቦችም፣ የኢለትሪክ ማመንጫዎችም፣ የባቡር መስመሩም፣ የቴሌኮም ዝርካታና ማስፋፍያውም ወዘተ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰዎችና ህዝቦች ሠሩት ይባላል። ገና በጣም ብዙ ይሰራሉ። በተባበረ ጥረታቸው ምክንያት ኢትዮጲያም የያዘችው የዕድገት ጎደና ይዛ ከመመንደግ ወደ ኋል የሚገታት ኃይል የለም። ተዘጋ መመለሻም የለውም።

## 8. "የሚኒሊክ አደራ አለብን"

የሸዋ ትምክህት ኃይሎችና የድሮ ገዢ መደቦች አንድ የሞኘ ዘፈን አላቸው። "የሚኒሊክ አደራ አለብን" ማለት ይደጋግማሉ። አፄ ሚኒልክ አደራ የተውላቸው ጉዳይ ምን ይሆን? የተውላቸው አደራ ሁሌም ከሰማይ የወረደው የነገስታትነት ስልጣናቸው እንዳይፈርስ መከላከል እንድችሉና የሸዋ ገዢ መደቦች የበላይነት ማረጋገጥ እንድችሉ ነው። ይህ ማለት የሸዋው ዘውዳው ሥርዓት ማስቀጠል እንዲችሉ ማለት ነው። የሀገሪቱ የፖለቲካ ስልጣን ከዚህ ሸዋዊ ሉህቃን (elite) እጅ አፈትልኮ በኢትዮጵያ ህዝቦች እጅ እናዳይገባ አቅማቸው አሟጥጠው መከላከል እንድችሉ ማለት ነው። በተለይ ደግሞ ስልጣን ከአፄ ሚኒሊክ ቤተ መንግስት አፈትልካ ወደ ህዝብ እጅ እንድትገባ ምክንያት ሊሆን የሚችል የትግራይ ህዝብ በኃይል ረግጦና ደፍጥጦ መያዝ ዋነኛ አደራቸው ነው። ይህን ህዝብ በድህነት አጎሳቅሎ ሞራሉን ገድሎ መኖር መቻል የአደራው ዋነኛ መልእክት ነው። ለዚህም ነው የትግራይ ህዝብ ከድህነት እንዳይወጣ አቅማቸውን አዋድደው በማያቋርጥ ሁኔታ እየሰሩ ያሉት። ያም ሆነ ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ከጫፍ እስከ ጫፍ በመተባበር በ1966 ዓ/ም ከሰማይ ወረደልን የተባለውን ዘውዳዊው አገዛዝ ከመሠረቱ ገንጥሎ ጣለ። ለሌላ ከፍተኛ መስዋዕት የሚጠይቅ የትግል ምዕራፍ ይዳርግህ ሲለው ሁላችንም እንደሚናውቀው የህዝቡ ስልጣን በወታደራዊው አምባገነን መንግስት እጅ ወደቀ። ይህንን መንግስት የሸዋው ገዢ መደባዊ ባህሪ እንድላበስ እነ ፕሮፌሰር መስፍን የመሳሰሉ የሸዋ ሉህቃን (elite) ጥረት ሳያደርጉ አልቀሩም። እናም በኢትዮጵያ ህዝቦች ያደረሰው አስከፊ ጭፍጨፋ እንደጠጠበቀ ሁኖ ፤ በተለየ ሁኔታ በትግራይ ህዝብ ላይ ጫና ያደርግ ነበረ።

በ1983 ዓ/ም ወታደራዊው አምባገነን መንግስት (ደርግ) በኢትዮጵያ ህዝቦች ከፍተኛ ተጋድሎ ምክንያት ከሀገሪቱ ምድር ተገረሰሰ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የአፄ ሚኒሊክ ባለ አደሮችና የደርግ ቅሪቶች አንድ የተባበረ ክንድ በመፍጠር በኢትዮጵያ ህዝቦች ፈቃደኝነትና አብሮ የመኖር ፍላጎት መሠረት የተመሰረተውን ህገ-መንግስታዊ ሥርዓት በኃይል ለመናድ እንሆ እስከ ዛሬ ቀን ከሌሊት ይለፋሉ። በህዝቦች ፍላጎት የፀደቀው ህገ መንግስት ህገ-አራዊት ነው ለማለት ደፈሩ። ምክንያቱም

እንደነሱ ህገ-መንግስት ከቤተ መንግስት ጓዳ ፀድቆ ከሰመይ የወረደ ነው ብለው የሰበኩልን መለኮታዊ ህገ-መንግስት አይደለምና።

ታድያ “ ዜጎች በተሳትፎአቸውና በፍቃዳቸው የመሠረቱት ህገ መንግስታዊ ሥርዓት በህገ ወጥ መንገድ ለመናጥ ለምን አስፈለገ? ህገ-መንግስቱ በበጎ ሁኔታ እየሰራ ባለበት ሁኔታና ሀገሪቱም ጥሩ የሆነ ሁለመናዊ ዕድገትና ለውጥ እያስመዘገበች ባለችበት ጊዜ በተለያየ መንገድና ጊዜ ነውጥ ማቀጣጠሉ ለምን አስፈለገ?” ብለው ጠየቁዋቸው። እነሱም “ይህን እናውቃለን ነገር ግን የሚኒሊክ አደራ አለብን።” ብለው መለሱ።

## 9. የታሪክ ምኞት

ታሪክ ለሁላችንም የማያሻማ ትርጉም አለው። ታሪክ በጊዜ፣ በቦታ፣ በሁኔታ በትክክል ተለይተው በጊዜ አቆጣጠር ተደርድረው የሚምመዘገቡ ህዝቦች የፈፀሟቸው ታላላቅ ተግባራት ስብስብ ነው። ፍፃሜዎቻቸው ብቻ ሳይሆን ህዝቦች አመጣጣቸው፣ ምንጫቸው፣ ባህላቸው፣ በየጊዜው የሚያዳብሩት የአናኗር ዘቤያቸው፣ ቋንቋቸውና የቋንቋቸው ዕድገት፣ ወዘተ ምንም ዛይዛባ እንደወረደ የሚመዘገብበት የኅብረተሰብ ጥናት ሳይንስ ነው። ታሪክ በዘፈቀደ በየፊናህ የሚትደሰኩረው ጉዳይ ሳይሆን በሞያው በሰለጠኑ ሰዎች ጥናትና ምርምር የሚደረግበት፣ የሚመዘገብ፣ በጥንቃቄ የሚፃፍና የሚጎለብት ጉዳይ ነው። ከዚህ ትርጓሜ አንፃር ስናየው የኢትዮጵያ ታሪክ በአገር ውስጥ ምሁራን በትክክል ልፃፍ አልቻለም። በዘፈቀደ ይደረደራል። ከማንነትህና ከበቀልክበት ብሔር ወይም ብሔረሰብ በማያያዝ ይደሰኮራል። ሞያዊ ስነ ምግባር በጎደለበት መልኩ ትክክለኛ መረጃ በማጠናቀር ሳይሆን ስሜትህ ወደ ነዳህ አቅጣጫ ታሪክ በማጣመም ይፃፋል፣ ይተረካል። በተለይ የሸዋ ገገር መደቦች የኢትዮጵያን ታሪክ ሆን ብለው በማጣመም የህዝቦች ታሪካዊ ተጋድሎ ለስማቸው መዘከረ ዝናቸው አድርገውታል። ከመንጥቅና ማጣመም ታልፎ በአንድ ህዝብ ላይ የማይገልፀውና ያልሆነውን ሲለጠፉለት ይስተዋላል።

አሁን፣ አሁንማ እንደነ ፍቅረ ቶለሳ (ፕሮፌ.) የተባለ ሰው ታሪኬ ይህ ቢሆን ብለው የሚመኙትን የታሪክ ምኞት መፃፍ ጀምረዋል። የራስህን ያልሆነ ታሪክ ጋር ራስህን ለማስተሳሰር የመመኮር ያክል ቀጣፊነትና የውርደት ውርደት የለም። ፍቅሬ ተሎሳ (ፕሮፌ.) የራሱን የዘር ሃረግ ከነ የመፅሃፍ ቅዶሶቹ አብርሃምና የኢየሱስ የዘር ግንድ ሊያስተሳስር መሞከሩ ግልፅ የታሪክ ምኞት ማሳያና የቀን ህልም ነው። እንደነዚህ ሰውዬ ያሉ የታሪክ ምኞተኞች በበዙበት ጊዜ ትክክለኛ የታሪክ መረጃ ከማግኘት ይልቅ የተወናበደ የታሪክ መረጃ ማግኘት ቀለዋል።

አንዳንድ ሰዎች ምዛናዊ በሚመስል መልኩ ታሪክን ኢትዮጵያዊ ቃና ለማልበስ ይሞክራሉ። ኢትዮጵያዊ ቃና ለማልበስ በሚል እዛም፣ እዚህም ሲዘባርቁ ደረቅ ውሸት ላይ ተዘፍቀው ታገኛቸዋለህ። ለምሳሌ ላጵሶ ጌታሁን ድሌቦ (ፕሮፌ.) የኢትዮጵያ ታሪክ - የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊያን የመነሻና የማንነት ግንዛቤ በሚል መፅሃፋቸው በአብዛኛው ሞያዊና በመረጃ የተደገፈ ቢሆንም ቂሉ በመሃል፣ በመሃል ኢትዮጵያዊ ቃና ለማላበስ በሚሞክሩበት ጊዜ የተፋለሰ ሆኖ ታገኘዋለህ። አንዳንዴም አውሮፓዊያን የፃፍሉን ታሪክ ስህተት መሆኑ ለማስረዳት ሲሞክሩ ማስረጃቸው ያልተሟላና አሳማኝነቱ አጣራጣሪ ሆኖ ታገኛዋለህ። አንዳንድ ግለሰዎችም ከመንጋው ወጥተው ትክክለኛውን ታሪክ ማስቀመጥ ሲጀምሩ በተለይ ከሸዋው ሉህቃን (elite) ወገን ትችትና መንጫጫትን ይፈጥራል።

ስለዚህ ኢትዮጵያዊያን የታሪክ ምሁራንና ፀሐፊዎች ትክክለኛ ታሪክ በድፍረትና ሞያዊ ስነ ምግባር በተሞላበት መንገድ መፃፍ ቢጀምሩ ህዝቦች ሊያስማማ እንደሚችል እገምታለሁኝ። የህዝቦችም የማንነት ምንጭ ይሁን ታሪካዊ ውሎቸው፣ በጋራ ነፃነታቸውን ለማረጋገጥ የፈፀምዋቸው ታሪካዊ ተጋድሎቸው፣ እንዲሁም የነገስታቶቻው ገድልም ይሁን እውነተኛ የዘር ሃረጋቸውና ማንነታቸው ሳይድበሰበስ ከነ ትክክለኛ አስረጂ መረጃው መቀመጥ አለበት። ትክክለኛና አሳማኝ መረጃ የሌላቸው ጉዳዮችም ትክክለኛ መረጃቸው ሳይንሳዊ መንገድ በተከተለ ምርምር መጠናቀር አለበት።

የሸዋ ልሁቃን በፈጠርዋቸው የተጣመሙ የታሪክ መዛግብት ምክንያት የትግራይ ህዝብን የማይገልፅ ስድቦች ሲሰነዘሩ አያለሁኝ። በማህበራዊ ሚድያና በተለያዩ ፅሁፎች “ከሃዲዎች” የሚል አፀያፊ ቃል አነባለሁኝ። በትግርኛ ሰዎች ራሳቸውን ሊሰደቡበት የሚገባ ስድብ ሌላው ላይ ሲለጥፉ “ተገልቢጡኒ” ይባላል። ነገሩ የተገላብጦሽ ነው ለማለት ነው። ከአፄ ቴድሮስ ዘመነ መንግስት በኋላ መሠረት ተደርገው በተፃፉ የኢትዮጵያ ታሪክ መዛግብት ውስጥ የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ ወደ ጎን የተው መሆናቸውን አንድ ጉዳይ ሆኖ፤ አንዳንድ የታሪክ ምኆተኞች ይባስ ብለው ይህን ህዝብ በክህደት ሊፈርጁት ይሞክራሉ። ይህ የሚባል መነሻ ግን የላቸውም። ነገሩ የተገላብጦሽ ነው።

ተጋሩና ኤርትራዊያን ወንድሞቻቸው ከአፄ ቴድሮስ ዘመነ መንግስት ጀምረው የውጭ ወራሪ ኃይሎችን ለመመከት ከፍተኛ መስዋዕት ከፍለዋል። በአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት ብዙ የውጭ ወራሪ ኃይሎች ሽንፈት ተከናንበው እንዲመለሱ አድርገዋል። በዚያን ጊዜ ነበር በአፄ ዮሃንስ ሰራዊት በራስ አሉላ አባነጋ ወታደራዊ አዛዥነት ግብፆች ተደጋጋሚ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንበው የተመለሱት፣ በዚያን ጊዜ ነበር ጣልያናዊያን በኤርትራ ምድር ላይ በተደጋጋሚ የተመቱት። በአፄ ዮሃንስ ጊዜ ነበር በኤርትራ በከረን አከባቢ ማሂድስት በትግራይና ኤርትራዊያን ጀግኖች ድባቅ ተመትቶ የተመለሰው። በዚህ ጦርነት ነበር ትግራይ እነ ሓንታ ገብሩን የመሳሰሉ የተዋጣላቸው ጀግኖች ልጆችዋ በመስዋዕት የከፈለችው። ይህ ሲሆን የሸዋ ገዢዎች የት ነበሩ? መሃል ሀገር ሁነው ጣይልያኖች ኢትዮጵያን እንዲወሩና በአፄ ዮሃንስ ላይ ጦራቸው እንድያዘምቱ ተንኮል ሲደሉቱ ነበር። ክህደት ማለት ይህ ነው።

አፄ ዮሃንስ የጎንደር ህዝበ በማህድስት ሲቃጠል ጣልያንን ትተው መተማ ላይ ሲዘምቱ ህዝባቸው የጎንደር ህዝብ ለማዳን ነበር። በዚህ ጦርነት ንጉሳቸውም ጨምረው ብዙ የትግራይ ተወላጆች መስዋዕት ሆነዋል። ዛሬ ልጆቻቸው ከጎንደር በትምክህተኞች ሰበብ ሲባረሩ ከመንግስተ ሰማያት ሆነው ሲመለከቱ ምን ያህል እያዘኑ እንደሚሆን ለመገመት አያዳግትም። የሰሜን ኢትዮጵያ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻቸው ለመከላከል ጎንደር ላይ ሲፋለሙ፤ አፄ ሚኒሊክና ግብረአበሮቻቸው ሸዋ ላይ ጥግያቸው ይዘው ስዝናኑ ነበር። ክህደት ማለት ይህ ነው።

አፄ ዮሃንስ መተማ ላይ መስዋዕት ከሆኑ በኋላ የጣልያን ጦር በተባባሪዎቹ በተፈጠረለት ዕድል ተጠቅሞ ኢትዮጵያን ለመውረር ሲገሰግስ ይህንን ወረራ ለመግታት የትግራይ ህዝብና ወንድሙ የሆነው የኤርትራ ህዝብ ከፍተኛ ፊልምያ ላይ በነበሩበት ጊዜ ከጎናቸው ማን ነበር? ማንም አልነበረም። ጣልያን ከቀይ ባህር ተነስቶ አምባአላጀ ተራራ ላይ እስከሚመሽግ ድረስ የተከፈለ መስዋዕት ላይ የሸዋ ገዢ መደቦች አልነበሩበትም። የሸዋ ገዢ መደቦች ልባቸው ለክህደት ቅርብ ነው። የትግራይ ህዝብ እየተፋለመ በደምብ እስከሚታሽላቸውና እስከሚዳከም ቁጭ ብለው ተዝናንተው ይመለከቱት ነበር። ክህደት ማለት ይህ ነው።

የጣልያን ወራሪ ኃይል ዓድዋ ላይ በተሸነፈበት ጊዜ ሙሉ ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት ራስ አሉላ አባነጋና ዕተጌ ጣይቱ ሃሳብ ሲያቀርቡ፤ ሃሳባቸውን ውድቅ ተርጎ ከትውልድ እስከ ትውልድ የማይረሳ ታላቅና አሳዛኝ ክህደት ተፈፀመ። ለዘመናት

የኢትዮጵያን ነፃነት ለማስከበር ከኢትዮጵያዊና ወገኑ ጎን ሆኖ ሲፋለም የኖረው ወንድም የኤርትራ ህዝብ ተጋሩን ለሁለት እንከፈል በሚል ተንኮል አሳልፈው ለባዕድ ሰጡት። ሆድ እያወቀ ደሮ ማታ እንዲሉ ኢህአዴግ ኤርትራን ገነጠለ ይሉናል። ትርጉም አልባ ዘፈንም ያንጎረጉራሉ።

ለሁለተኛ ጊዜ ጣልያን አገራችንን ሲወር፤ የጣልያን ሰራዊት ከኤርትራ ጠረፍ ተነስቶ ማይጨው እስከሚደርስ ድረስ ወረራውን ለመግታት የትግራይ ህዝብ አሁንም ከፍተኛ መስዋዕት ከፈለ። የአፄ ሃይለስላሴ ጦር ከጎኑ አልነበረም። አፄ ሃይለስላሴ ምንም ሳይዋጉ ከማይጨው ሲፈረጥጡም የደቡብ ትግራይ ህዝብ መፈርጠጥ የለበዎትም በሚል ተቃውሞውን አሰምተዋል። ከዛም በኋላ እንደነ በላይ ዘለቀ የመሳሰሉት ጀግኖች ኢትዮጳያዊያን መሃል አገር ጣልያን በማስጨነቅ በነበሩበት ጊዜ የትግራይ አርበኞችም ትግራይ ውስጥ ከፍተኛ የአርበኝነት ትግል ያካሁዱ ነበር። አፄ ሃይለስላሴ በላይ ዘለቀን ሰቅለው እንደገደሉት ፤ ለዓመታት ጣልያን ሲፋለም የነበር የትግራይ ህዝብ በመጀመርያ ወያኔ አምፃችኋል በሚል ሰበብ የባዕድ ተዋጊ አውሮፐላና ች በመጠቀም የመቀሌና የደቡብ ትግራይ ሰላማዊ ህዝብ ብቀላ ይመስል በግፍ ደበደቡት። ክህደት ማለት ይህ ነው።

በደርግ ዘመን ሶማልያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ጊዜም ከትግራይ የተመለመሉ ታጣቂ ምልሽዎች ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጎን በመሰለፍ ከፍተኛ ገድል ፈፅመዋል። የኡጋደን ውሎአቸው ምን ያህል ወሳኝ እንደነበር መንግስቱ ኃ/ማርያም ለህናው ቢመሰክር ጥሩ ነበረ።

ለማንኛውም ህዝብ አይከድም። ገዢ መደቦችና ግለሰቦች ሊከዱ ይችላሉ። ሁሌም ህዝብ ሚዛኑ እንደጠበቀ ነው። ሚዛኑ በሃሰትና በውዥንብር አይናድም። ዛሬ ጎንደር ውስጥ በተፈፀመው ግፍ የአማራ ህዝብ ፍላጎት አይደለም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች ፍላጎት እንጂ። የአማራ ህዝብ ከሃዲ አይደለም። በተለይ ደግሞ ወገኑ ለሆነው ለትግራይ ህዝብ አይከድም። የትግራይና የኤርትራ ህዝብ ለመለያየት ፍፁም ክህደት የፈፀሙት አፄ ሚኒልክና ግብረ አበሮቻቸው ነበሩ። የጎንደር ህዝብ በማሂድስት በተጠቃበት ጊዜ አስቀያሚ ክህደት የፈፀሙት ዳግምዊ አፄ ሚኒልክና ከሳቸው ጎራ የተሰለፉት የስልጣን ጥማቶኞች ነበሩ። በመሠረቱ የአማራ ህዝብ ከሃዲ ቢሆን ኖሮ አፄ ዮሃንስ ለጎንደር ህዝብ ሲሉ መተማ ላይ አንገታቸው ባልሰጡ ነበር። ኤርትራና ትግራይ ለመውረር በተጠንቀቅ የቆመውን የጣልያን ኃይል አስቀድመው በመከቱ ነበር። ነገር ግን በወቅቱ ጎንደር በማሂድስት ስትቃጠል ፤ ጊዜ የሚሰጥ ሆኖ አላገኙትም። ጊዜ የሰጣቸው ለሸዋ ነገስታት ነበር።

ከ1981 ዓ/ም እስከ 1983 ዓ/ም ደርግን ለመደምሰስ በመሃል አገር በነበረው ትንቅንቅ የተሞላበት የትግል አውድ የትግራይና የአማራ ህዝብ ተቆራኝተው ከፍተኛ መስዋእት ከፍለዋል። በደብረታወር በጉና፣ በጉጉፍና የመሳሰሉ ውግያዎች አብረው ደምተዋል፣ አብረው ተቀብረዋል። በዚያን ጊዜ የአማራ ህዝብ ትግሉን በመደገፍ ፍቅር በተሞላበት ታጋዮችን በማጥለል፣ ቁስላቸውን በማከም፣ ከወደቁበት በማንሳት፣ ከጠላት ጥቃት በመሰወር ወደር የሌለው ታሪክ ፈፅመዋል።

የኦሮሞ ህዝብም ቢሆን በትግራይ ህዝብ ላይ ጥላቻ የለውም። ህዝብ በማንም ህዝብ ላይ ጥላቻ አይኖሮውም ። ሊኖሮውም አይገባም። አመናችሁም አላመናችሁም በህዝብ መሃከል የሚጋጥም ችግር በአመራሮችና በፖለቲከኞች ምክንያት በሚፈጠር ስህተት ነው። የሩዋንዳውም የዘር ማጥፋት ወንጀል የህዝብ ለህዝብ ሳይሆን የፖለቲከኞች ችግር ነው። አጥፊ ኃይሎች የውሸት ታሪክ ቢደሰኮርም፣ የጥላቻ ንግግር ቢረጩም ህዝብ በህዝብ ላይ አልተነሳም። ባልበሰሉ ወጣቶች ዘርን መሰረት ያደረገ ጥቃት በተለያዩ ቦታዎ ች ተፈፅመዋል። ይህን ተግባር ግን በኔ እምነት ፈፅሞ ህዝቡን አይወክልም። ለማኛውም ህዝብ በህዝብ ላይ አይነሳም ህዝብም ክህደት አይፈፅምም።

## 10. የ“ትግራይ ልትገነጠል  ነው” ውዥምብር

የሶሻል ሚድያ የአልቧልታ ጥበበኞች  የ“ትግራይ ልትገነጠል ነው”  ጉዳይ “አንድ ምሁር አሉ” በሚል ብዙ እያናፈሱ ይገኛሉ። ተጋሩ ማንነታቸው ላይ አነጣጥሮ  ለደረሰባቸው ጥቃት ደስታቸው ሲገልፁ ነበር። በየአከባቢው ለደረሰበት ግድያ፣ ከቤት ንብረቱ መፈናቀልና ኢሰብአዊ ድርግት ለማውገዝ ሞራል የሌላቸው ሂሊና ቢሶች ትግራይ ውስጥ እፍኝ አፈር አለን ብለው ይሞግታሉ። እኛ ትግራይ ውስጥ እፍኝ አፈር ሲኖረን እንዴት ተጋሩ ጎንደር ውስጥ እፍኝ አፈር አይኖራቸውም ብለው  እንኳ ትንሽ ዞር አርገው  ማሰብ አልቻሉም። እኛ ትግራይ ውስጥ መሬት አለን፤ እናንተ ግን ጎንደርና ወልድያ መሬት የላችሁም ይሉናል። ትግራይ የጋራችን፤ ጎንደር የብቻችን ይመስል።

የግዛት አንድነት ሰባኪዎች ለነሱ ሀገር ማለት ወንዙ፣ ተራራው፣ ሸንተረሩ፣ ሜዳው የያዘው የተፈጥሮ አከባቢ (natural environment) ነው።  በዚህ የተፈጥሮ  አከባቢ ኑሮው መሠረት አድርጎ ለዘመናት የሰፈረው ክቡር ማህበረሰብ (social organization) ምናቸው አይደለም። አንድ የተፈጥሮ አከባቢ አቅፎ የያዘውን ክቡር የሰው ልጅ ዋጋ ሳይሰጡ እንዴት ነው ስለ አንድነት መነጋገር የሚቻለው። ጋዜጠኛ የትነበርከ ታደለ የተባለ ሰው በፌስ ቡክ ገፁ አሰፈረው የተባለው የቡራከራዩ ፅሁፍ አንዳንድ ዐረፍት ነገሮቹ ቀንጭቤ ሃሳቤ  ላጋራችሁ። የትነበርከ ታደለ “ትግራይ ‘ኮ የትግራይ ብቻ አደለችም።. . . ” ይላል። አዎ! ነገር ግን ትግራይ የጋራ መሬታችን የሚትሆነው ፣ የትነበርከ ታደለ  ጎንደርም የጋራ መሬታችን መሆንዋ ማመንና  በተግባር ማዋል ከቻለ ብቻ  ነው።  አለበለዚያ የትነበርከ “ጎንደር የብቻዬ፤ ትግራይ የጋራችን ።”  ብሎ መከራከር የሚችልበት ጭብጥ ወይም መሠረተ ሃሳብ አይኖሮውም። ኢትዮጵያ የጋራ ሀገራችን፣ መኖርያችን እስከሆነች ድረስ ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ  መሥራት፣ መኖር ይችላል። ቢሆንም ቅሉ በነ የትነበርከ ታደለ ጎራ ግን ይህን እሴት የሚንድ አፀያፊ ተግባር እንየተፈፀመ  ይገኛል።

ቀጥሎም “የጥንቱ የታሪክ አሻራ . . . የትናንቱ ባድመ ” ወዘተ ይላል። አንድ የስነ ልቦና ምሁር እንዳስነበበን አንዲት የተረት ወፍ ነበረች። ያቺ ወፍ የሚትጥለው ዕንቁላል ወርቅ ነበረ። አንድ ሰው ወርቁን ለመጠቀም ከፈለገ ወፍዋን ችላ ማለት አለበት ወይ ነው ጥያቄው። የጋዜጠኛው ሃሳብ ወርቁን እፈልጋለሁኝ፤ ወፍዋን ግን እገድላለሁኝ ይመስላል። ጋዜጠኛው የትግራይ ህዝብ ልጆች ያሳድዳል፤ የትግራይ መሬትና  ትግራይ ውስጥ ያለው የታሪክ አሻራዎች ግን ይፈልጋል። ከታሪክ ስግብግብነት ይልቅ የህዝብ ወገንተኝነቱ ማስቀደም ብስለትና ሰብአዊ አስተሳሰብ አይደለም ወይ? ለታሪክ ከሆነ የጋዜጠኛው ጭንቀት፤ የትግራይ ህዝብ መተማ ላይ ታላቅ የታሪክ አሻራ አኑሯል። በምስራቅ ኢትዮጵያም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን ወገኖቹ ጎን ተሰልፎ  ታላቅ ገድል ፈፅመዋል። ዛሬ ደግሞ  ከኢትዮጵያዊያን ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝብ አንዱ እስከመሆኑ ድረስ የህዳሴ  ግድብ ላይ አሻራውን እያኖረ ይገኛል። ቢገነጠል ይህን ሁላ ድካሙና ውጤቱ ትቶ ነው የሚገነጠል። ስለዝህ አይበለውና  ነገሩ ሰጥቶ መቀበል ነው።

ሌላው  ጋዜጠኛ የትነበርከ ታደለ የፃፈው ዓረፍተ ነገር እንድህ ይላል “ . . . የኢትዮጵያ  ህዝብ ከንግድህ ከደንበሩ ቁርሶ የሚሰጠው መሬት ይቅርና  እፍኝ አፈር የለም።”  ፈጣሪ እዛ ደረጃ  አያድርሰን እንጂ ጋዜጠኛው እፍን አፈር ይቅርና የሰናፍጨ ቅንጣት የሚታህል አፈር እንኳ እንደማያገኝ ልቡ ያውቀዋል። ጋዜጠኛው በአስተሳሰብ ደረጃ የትግራይ ህዝብ የራሱ ዕድል በራሱ የመወሰን ህገ መንግስታዊ መብቱ በጉልበት ለመግታት መሞከሩ ነው። ነገሩ የሽሮ  ድንፋታ ውሃ እስኪገባበት ድረስ ቢሆንም ፤ በትግራይ ህዝብ ዕድል ማንም መወሰንና ዕድሉ መገደብ አይችልም። ይህን መብት በህገ

መንግስቱ በማያዳግም የተቀመጠ ነገር ነው። ብሔር፣ ብሔረሰብና ህዝቦች ለትግራይ ህዝብ ብለው አይደለም የደነገጉት - ህዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸውን ለመወሰን እንዲችሉ እንጂ።

የጋዜጠኛው ፍኮራና ማቅራራት ወደ ጎን እንተዎውና እኔ እንደ ሰው ከመገነጣጠል ይልቅ አብሮነትን መርጣሎህ። ኢትዮጵያዊያን በዕኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ ሆነው የመሠረቱት የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የበለጠ አብሮነቱ ማረጋገጥ እንዲችል ሰላምን በማረጋገጥ ረገድ ጠንክረው መሥራት አለባቸው። ይህ ታልቅ ህዝብ የጥላቻ ፖለቲከኞች ፕሮፓጋንዳ ወደ ጎኖ ትቶ ሰላሙን ጠብቆ ዲሞክራሲያዊ ስርዓቱን ማስኬድ ከቻለ በኢኮኖሚ የበለፀገች፣ ለሌሎች የሚትተርፍ ታላቅ ሀገር መገንባት ይችላል። ከላይ የጠቀስኳቸው ጠላቶቹ መከላከል ከቻለ ይህ እውን እንደሚሆን የሚያጠራጥር ነገር የለውም። ኢትዮጵያ የራስዋን አንድነትና ትስስር አጠናክራ ከጎሮቤት ሀገሮች ፍትሃዊነትና የጋራ ተጠቃሚነት መርህ የተከተለ የኢኮኖሚ ትስስር መፍጠር ከቻለች የቀጠናው ብልፅግናም ይረጋገጣል።

የ“ትግራይ ልትገነጠል ነው” ጉዳይ ከውኘምብር ያለፈ ጉዳይ አይመስለኝም። የትግራይ ህዝብ የእገነጠላሎህ ጥያቄ ሊኖሮው አይችልም። ተወደደም ተጠላም ትግራይ የኢትዮጵያ መሠረት ናት። መሠረቱ የተናጠ ነገር ቆሞ መኖር አይችልም። ኢትዮጵያ በዛፍ ከመሰልናት የዛፉ ሥርና ግንድ ትግራይ ውስጥ ነው ያለው። ይህ ማለት ትግራይ ኢትዮጵያም ትግራይም ናት። ስለዚ ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ወዴት ትውጣ? ቢገነጠል ቅርንጫፍ ይገንጠል እንጂ ሥርና ግንድ ወዴት ይገንጠል - የተገነጠለ እንደሆነ የዛፉ መጨረሻ ስለሚሆን።

ሰላምና ብልፅግና ለኢትዮጵያ!

ማወቅ ይበጃል ነኝ። ድምፅዬን ለሰማኝ ሁሉ ከወዲሁ አመስግናሎህ!

(ፅሁፉን አስመልክታችሁ የሚትሉኝ ካለ በ maweqyibejal@gmail.com ልታገኙኝ ትችላላችሁ)።